ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዘመናት ፡ ከቈየ ፡ ሞግዚትነት ፡
በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ትጋት ፡ የተገኘ ፡

# የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስና ፡ ነጻ ፡ መሆን ።

✶

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ፡ ኻያ ፡ አምስተኛ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ (ኢዮቤል ፡)


በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ከኒከላኦስ ፡ ግሪክ-ኦርቶዶክስ ፡ የአክሱም ፡ ሜትሮፖሊት ፡
ተዘጋጀ ።

◆◆◆

አዲስ ፡ አበባ ፤ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡

www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፤
(አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ።)

www.ethiopianorthodox.org

ስለ፡ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኀሩይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
መታሰቢያ ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፥
ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ።

(ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡)
(ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

www.ethiopianorthodox.org

ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ ነጻ ፡ መንግሥትኛ፥
ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የታሪኳን ፡ ዕድል ፡ ለተከታተለው ፡ ኹሉ ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ የዘውድ ፡ የብር ፡ ኢዮቤል ፡ በነዚህ ፡ በኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በዚህች ፡ ጥንታዊት ፡ በኾነች ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመውን ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ያስታውሰዋል ።

እነዚህም ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ የኢትዮጵያ ውያንን ፡ ኑሮ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲኾኑ ፡ ሥራዎቹ ፡ ፍጻሜ ፡ ያገኙት ፡ እሊህ ፡ ገናና ፡ መሪ ፡ ከውጭም ፡ ከውስጥም ፡ የገጠሟቸውን ፡ ተቃዋሚዎችና ፡ አያሌ ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ ጠንክረው ፡ በመታገል ፡ በሕዝቡና ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ በነዙት ፡ የሥራና ፡ የመሻሻል ፡ መንፈስ ፡ ብርታት ፡ ነው ።

ሀገሪቷን ፡ የሚመለከተውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ረቂቅ ፡ ዘዴና ፡ በማያወላውለው ፡ ጽኑ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ዕንቅፋቶቹና ፡ ተቃዋሚዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ተደምስሰው ፡ ተወገዱ ።

ኾኖም ፡ የፍጡርን ፡ ዕድል ፡ የሚጨብጠው ፡ አምላክ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ እንደ ፡ ጠበቀና ፡ ጥረታቸውም ፡ ፍሬ ፡ እንዲያገኝ ፡ እንደ ፡ መሪቸው ፡ አለመርሳት ፡ ይገባናል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ እርምጃው ፡ እየገፋ ፡ እንዲኼድ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ ድካም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ባርኳል ። በዚህች ፡ አፍሪቃዊት ፡ በኾነችው ፡ ሀገር ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የተቀበሉትን ፡ ከፍተኛ ፡ አደራ ፡ ከመልካም ፡ ግብ ፡ እንዲያደርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርታትን ፡ ሰጥቷቸዋል ።

ከነዚህም ፡ የሕዝቡን ፡ ብሔራዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ኹኔታን ፡ ለማሻሻል ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ከፈጸሟቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በሞግዚት ፡ መተዳደሯ ፡ ቀርቶ ፡ «በነጻ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡» እንድትኾን ፡ የደከሙት ፡ ድካም ፡ ነው ።

ይህም ፡ ጉዳይ ፡ በተለመደውና ፡ በታወቀው ፡ ንጉሣዊ ፡ ዘዴና ፡ በዲፕሎማሲ ፡ ችሎታቸው ፡ ፍጻሜ ፡ አግኝቷል ። ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራሷን ፡ ለማስተዳደር ፡ ባገኘችው ፡ የነጻነት ፡ ደረጃና ፡ ራሷን ፡ ወደ ፡ መቻል ፡ ደረጃ ፡ በመራመድ ፡ ላይ ፡ በመገኘቷ ፡ መኩራት ፡ ይገባታል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የመኾኗ ፡ ነገር ፡ ረዥም ፡ ታሪክ ፡ አለው ።

ይህም ፡ ሞግዚትነት ፡ የተገለመረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ በተባለው ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ በኢትዮ

www.ethiopianorthodox.org

ጵያ ፡ ክርስትና ፡ ከተሰበከና ፡ እርሱም ፡ ራሱ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጳጳሷ ፡ ሆኖ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ከተሾመበት ፡ ከ፫፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (1.) ወዲህ ፡ ነው ።


ኢትዮጵያ ፡ ክርስትናን ፡ በተቀበለችበት ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥር ፡ መተዳደሯ ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርይ ፡ በተነሣው ፡ ክርክርና ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ምክንያት ፡ ምሥራቃዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተበጣበጠች ። ይህም ፡ ብጥብጥ ፡ በምድረ ፡ ምስር ፡ ውስጥ ፡ መፋለስን ፡ ፈጥሮ ፡ መለካዊና ፡ ያዕቆባዊ ፡ የተባሉትን ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ አስነሣ ። በዛሬው ፡ ዘመን ፡ አነጋገር ፡ መጀመሪያው ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሁለተኛው ፡ የቅብጥ ፡ (የኮፕት) ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይባላሉ ።

እነዚህም ፡ በምስር ፡ የነበሩት ፡ መለካዊትና ፡ ያዕቆባዊት ፡ ወይም ፡ ቅብጣዊት ፡ (ኮፕት) ፡ (2.) የተባሉት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁለቱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እናትነትና ፡ ሞግዚትነት ፡ ለኛ ፡ ይገባናል ፡ ሲሉ ፡ ተከራከሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ በአክሱምና ፡ በቊስጥንጥንያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ወዳጅነትና ፡ የፖለቲካ ፡ ግንኙነት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከቅብጣዊት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ መለካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድታዘነብል ፡ አደረጋት ። ለዚህም ፡ የታሪክ ፡ ማስረጃ ፡ ይገኛል ።

ኾኖም ፡ በሰባተኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በምስርና ፡ በጠቅላላው ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ሀገሮች ፡ ሰፊና ፡ ዘላቂ ፡ የኾነ ፡ የፖለቲካ ፡ መለዋወጥ ፡ ደረሰ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመኻከለኛው ፡ ባሕር ፡ አካባቢ ፡ ካለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ የነበራት ፡ መገናኛ ፡ ተቋረጠ ። በዚህም ፡ እክል ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለፈቃዷ ፡ በያዕቆባዊት ፡ (ቅብጣዊት) ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ገባች ። በልማድም ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃ ፡ በቅብጣዊት ፡ ፓትርያርክ ፡ የሚሾመው ፡

1.—በዚህ ፡ ጽሕፈት ፡ የሚጠቀሰው ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኹሉ ፡ እንዳውሮጳያውን ፡ አቈጣጠር ፡ ነው ።

2.—በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ካሉት ፡ ኦርቶዶክሳውያት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንዷ ፡ መለካዊት ፡ የተባለችበት ፡ ምክንያት ፡ የቊስጥንጥንያ ፡ ንጉሥ ፡ (መለክ) ፡ የተቀበለውን ፡ እምነትና ፡ ሥርዓት ፡ በጥብቅ ፡ ይዛለች ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ነው ፡ እንደኛይቱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያዕቆባዊት ፡ የተባለችበት ፡ ምክንያት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ በምስርና ፡ በሶርያ ፡ በሜስጶጦሚያም ፡ የነበሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከግሪክና ፡ ከላቲን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈልሰው ፡ የተዋሕዶን ፡ እምነት ፡ እንዲይዙ ፡ ያሳበራቸውና ፡ የመራቸው ፡ ባሕታዊ ፡ ስሙ ፡ ያዕቆብ ፡ ባራዴአስ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ። ይህ ፡ የተዋሕዶ ፡ እምነት ፡ አሳባሪና ፡ መሪ ፡ ባራዴአስ ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ የነበረው ፡ ሀብቱ ፡ በሙሉ ፡ ባርዳታ ፡ የተባለ ፡ ከፈረስ ፡ ጠጕር ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ነው ፡ ግማሹን ፡ ይለብሰው ፡ ግማሹን ፡ ደግሞ ፡ እንጥሮ ፡ ይተኛበት ፡ ነበር ።



ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መናገሻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ኾነ ።



ብፁዕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከአክሱም ፡ ሜትሮፖሊትና ፡ ከሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ።

www.ethiopianorthodox.org

ከምስር ፡ ከቅብጦች ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ መካከል ፡ እየተመረጠ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ተያይዞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ መባል ፡ ደረሰች ።

ምንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃዋን ፡ ከቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብትቀበል ፡ በመንፈሳዊና ፡ በታሪክ ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ቅብጦች ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ የራሷ ፡ ባህል ፡ ያላት ፡ ብሔራዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ኾነችና ፡ ለሕዝቡም ፡ ብሔራዊ ፡ መንፈሱን ፡ የሚገልጽበት ፡ መሣሪያው ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ ነው ። የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብጣዊት ፡ የሚል ፡ ኹሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክና ፡ የሕዝቡን ፡ ክልብ ፡ የኾነውን ፡ ብሔራዊ ፡ መንፈሱን ፡ ያልተገነዘበ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልዩና ፡ የግል ፡ የኾነ ፡ የራሷ ፡ ጠባይ ፡ ያላት ፡ የጥንታዊቱ ፡ ምሥራቃዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ናት ። ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ የራሷ ፡ ወግና ፡ ሌሎችም ፡ ከቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚለዩዋት ፡ ብዙ ፡ ምልክቶች ፡ አሏት ። በማእከላይ ፡ ባሕር ፡ አውራጃ ፡ ከነበረችው ፡ ከግሪክና ፡ ከላቲን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተለይታ ፡ በኖረችበት ፡ አያሌ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በራሷ ፡ ብሔራዊ ፡ ባህል ፡ ተመሥርታና ፡ ተመርታ ፡ ያደገች ፡ ናት ። በዚህም ፡ ረዥም ፡ በኾነውና ፡ ዝርዝር ፡ ታሪኩም ፡ ባልታወቀበት ፡ የብቻነት ፡ ኑሮ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ከውጭው ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ የነበራት ፡ መገናኛ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ነበር ። ዐረቦች ፡ ምድረ ፡ ምስርን ፡ ከወረሩ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ መገናኛዋ ፡ ከቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ ገዳም ፡ ተመርጦና ፡ ተሹሞ ፡ የሚላክላት ፡ ቅብጣዊ ፡ ጳጳስ ፡ ኾነ ። ምን ፡ ጊዜም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከአንድ ፡ ጳጳስ ፡ የበለጠ ፡ አልነበራትም ፤ እርሱም ፡ ሲሞት ፡ የምስር ፡ መንፈሳዊና ፡ ብሔራውያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዜና ፡ ሞቱን ፡ ሰምተው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ አቡን ፡ እስኪልኩ ፡ ድረስ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ረዥም ፡ ዓመታት ፡ ያልፉ ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ የመኾኗ ፡ ምልክት ፡ ይኸው ፡ የሞግዚቷ ፡ እንደራሴ ፡ የኾነው ፡ ጳጳስ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

ይህ ፡ ሞግዚትነት ፡ ብዙ ፡ ደረጃ ፡ ነበረው ፤ ብዙ ፡ እክልም ፡ አጋጥሞታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአቡኑ ፡ አማካይነት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ በነበራት ፡ ግንኙነት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ተጠቀመች ፡ ወይም ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ተጐዳች ፡ ማመዛዘን ፡ የዚህ ፡ ጽሕፈት ፡



ጕዳይ ፡ ባይኾን ፡ ስንኳ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ እናቲቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለልጅቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትሰጣት ፡ የምትችለው ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አያዳግትም ።

ክርክር ፡ የሌለበት ፡ ኾኖ ፡ የሚገኘው ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመንፈሳዊው ፡ እንደራሴው ፡ አማካይነት ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ በመንግሥቱ ፡ እንደራሴው ፡ አማካይነት ፡ በፍጹም ፡ ነጻ ፡ ለመኾን ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነቱን ፡ አኳኋን ፡ ለመለወጥ ፡ በብርቱ ፡ መታገሉ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በነጻነቷና ፡ ራሷን ፡ በማስተዳደር ፡ ደርጅታ ፡ ነጻነቷንም ፡ በመጠበቅ ፡ በጠነከረች ፡ መጠን ፤ እንደዚሁም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንዋም ፡ ራሷን ፡ እንድታስተዳድር ፡ ነጻም ፡ እንድትኾን ፡ ትጣጣር ፡ ነበር ። ኢትዮጵያውያን ፡ ያላቸው ፡ ጠንካራ ፡ ብሔራዊ ፡ መንፈስ ፡ ሲታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ያን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ኾና ፡ መቈየቷ ፡ የሚገርም ፡ ነው ።

በነጻ ፡ ሀገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማግኘት ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብርቱ ፡ ምኞቱ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንፈሳዊ ፡ ሞግዚትነት ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነቱን ፡ ግንኙነት ፡ ለማሻሻል ፡ ይህ ፡ ምኞት ፡ በየጊዜው ፡ የተገለጸበትን ፡ ታሪክ ፡ ለጊዜው ፡ እንለፈው ።

በመንፈሳዊም ፡ ረገድ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በፖሊቲካ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረገውን ፡ እርምጃ ፡ በጥንቃቄና ፡ ያለአድልዎ ፡ የተከታተለ ፡ ኹሉ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያደረጉትን ፡ ጥረት ፡ ሳያስታውሰው ፡ አይቀርም ። እንደ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐሳብ ፡ ምንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በናቷ ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ኾና ፡ መቈየቷ ፡ ለቀድሞው ፡ ዘመን ፡ የተገባ ፡ ቢኾን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ምእመናኑ ፡ ስለ ፡ በዙ ፤ ሰበካውም ፡ በጆኦግራፊያ ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ሰፋ ፡ የጳጳሳቱ ፡ ቍጥር ፡ ማነሱና ፡ ከማነሱም ፡ በቀር ፡ ሥልጣኑ ፡ የተገደበ ፡ መኾኑ ፡ ይልቁንም ፡ የአቡኑ ፡ መንበር ፡ በየጊዜው ፡ ባዶ ፡ እየኾነ ፡ መቈየቱ ፡ ሰፊ ፡ ለኾነው ፡ ሀገራቸው ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾኗል ፡ የማለት ፡ ሐሳብ ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ ብዙ ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ ለጋራ ፡ የተያዘው ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናትና ፡ ትጋት ፡ ወጣ ፡ ወረድ ፡ ኾኖ ፡ ነበር ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የአቡነ ፡ አትናቴዎስን ፡ ዕረፍት ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፤ የጳጳሳቱን ፡ ቍጥር ፡ ለማበርከትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ሁኔታ ፡ ለማደራጀት ፡ ተነሡ ። ቅብጣዊቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን ፡ ጥያቄያቸውን ፡ ከልፈጸመች ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ለመቃረብ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አድርገው ፡ ነበር ። (3.)

ከላይ ፡ እንዳልነው ፡ ይህ ፡ የአፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጥያቄ ፡ ከሀገሩ ፡ ምኞት ፡ ጋራ ፡ የተዋሐደ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። አፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ማስፈራራታቸው ፡ ፍሬ ፡ አግኝቶ ፡ አራት ፡ ቅብጣውያን ፡ ጳጳሳት ፡ አሾሙ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጳጳሳቱ ፡ ቍጥር ፡ ባራት ፡ የተወሰነው ፡ ላራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ ምሳሌ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ።

አንዱ ፡ ጳጳስ ፡ በትግሬ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ከንጉሡ ፡ አቅራቢያ ፡ እንዲኖር ፡ አንዱ ፡ ለጎጃም ፡ አንዱ ፡ ለሸዋ ፡ ኾኖ ፡ አራተኛው ፡ ልጃቸውን ፡ ሊልኩለት ፡ ላሰቡት ፡ ንጉሣዊ ፡ ግዛት ፡ ተመድቦ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መጨረሻው ፡ ምኞት ፡ በአፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የአርበኝነት ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀረ ።

ከነዚህ ፡ ከራቱ ፡ ጳጳሳት ፡ በጨ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ ብቻ ፡ በሕይወት ፡ ተገኙ ። ብዙ ፡ ዘመንም ፡ ለስብከታቸውና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ታማኝ ፡ ኾነው ፡ ኖሩ ። አጭር ፡ በኾነው ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥትና ፡ በጊዜውም ፡ የኾነው ፡ ሁሉ ፡ አደራውን ፡ ያወቁና ፡ አደራውን ፡ የጠበቁ ፡ አቡን ፡ መኾናቸው ፡ ምንኛ ፡ እንደሚጠቅም ፡ አስታወቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ጉዳይና ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሞግዚትነት ፡ ከአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ በኋላ ፡ በበረታ ፡ አኳኋን ፡ ተነሣ ። ከትግሉም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ የተነሣው ፡ አዲሱ ፡ ክክብ ፡ በጥብቅና ፡ በቈራጥነት ፡ ገባበት ። ግርማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ከሚባሉበትና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ገምሮ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በጠንካራ ፡ እጃቸው ፡ ጨበጡት ። የመንግሥቱን ፡ አስተዳደር ፡ ለማሻሻልና ፡ ለማደራጀት ፡ ፕሮግራማቸውን ፡ ሲወጥኑ ፡ ለዚህ ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ ገምሮ ፡ ሲጓተት ፡ ለመጣው ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉዳይ ፡ የሚገባ ፡ አስተያየትና ፡ ሥፍራውን ፡ ሰጡት ።

የሕዝብ ፡ ገገሮችና ፡ መሪዎች ፡ ታላቅ ፡ የመባላቸውና ፡ ድካማቸውም ፡ ፍሬ ፡ የማግኘቱ ፡ ነገር ፡ በኀላፊነታቸውና ፡ በመሪነታቸው ፡ ሥር ፡ የሚተዳደረውን ፡ ሕዝባቸውን ፡ ቅን ፡ ግቡንና ፡ ምኞቱን ፡ ችግሩንም ፡ ከማቀፋቸው ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

---

3.— ለማስፈራራትም ፡ ሲሉ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅና ፡ ከእስክንድርያው ፡ የግሪክ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ሦፍንዮስ ፡ ጋራ ፡ መላላክ ፡ ገምረው ፡ ነበር ። የግሪኩ ፡ ንጉሥና ፡ ፓትርያርኩ ፡ መልስ ፡ ላለመስጠታቸው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለማናገኝላቸው ፡ ያሳዝናል ።



ከጥንት ፡ ገምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሃይማኖትና ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂ ፡ ኾኖ ፡ ይታያል ። ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ንጉሥ ፡ በየጊዜው ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲስፋፋ ፡ አድርጓል ። እንዲያውም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭም ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስትናን ፡ ጠብቋል ። የዚህም ፡ ማስረጃ ፡ ኤል ፡ አጽብሐ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ለመጠበቅና ፡ ድሁነምስ ፡ የተባለው ፡ ይሁዳዊ ፡ ዐረብ ፡ ናግራን ፡ ላይ ፡ በሰፈው ፡ ያፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ በአርበኝነት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ዐረብ ፡ መዝመቱ ፡ ነው ። (4.)

የንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተከራካሪ ፡ የመኾኑ ፡ ነገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ቤተ ፡ መንግሥትን ፡ አቃረበ ፤ በጥብቅም ፡ አስተሳሰረ ። በመካከላቸውም ፡ የወሮታ ፡ ሰንሰለትን ፡ ዘረጋ ። ይህም ፡ አንዳንዶች ፡ በስሕተት ፡ እንደሚሉት ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባርነት ፡ ገባች ፡ ማለት ፡ አይዶለም ።

በቍስጥንጥንያም ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ የወሮታና ፡ የመረዳዳት ፡ መንፈስ ፡ ነበር ። እዚያም ፡ ቢኾን ፡ አንዳንዶች ፡ ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ ሳይገምቱት ፡ ቀርተዋል ። ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብሔራዊ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለች ፡ ቍጥር ፡ ከቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ጋራ ፡ ተባብሮ ፡ የመሥራት ፡ ነገር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ። በምሥራቅ ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ ዐይነተኛ ፡ ሁኔታ ፡ ይገኛል ። ለምዕራባውያን ፡ ሀገሮች ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አስተያየት ፡ እንግም ፡ አይገባቸውም ። በምዕራባውያን ፡ ዘንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሕዝብ ፡ የነጻነት ፡ አርምጃ ፡ ዕንቅፋት ፡ የኾነችበትና ፡ የሕዝብን ፡ የኪነ ፡ ጥበብና ፡ የሀላዊ ፡ እርምጃን ፡ የተቃወመችበት ፡ ዘመን ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ምሥራቃውያንንና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሚነቅፉ ፡ ኹሉ ፡ ተሳስተዋል ።


ግርማዊነታቸው ፡ የወጠኑት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማሻሻል ፡ ሥራ ፡ ከውጭና ፡ ከአገርም ፡ ውስጥ ፡ ተቃዋሚ ፡ አለማጣቱ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። የፖሊቲካ ፡ ሥራ ፡ ከገመሩበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ተነሥተውባቸው ፡ ነበር ። ግርማዊነታቸው ፡ ግን ፡ በትዕግሥት ፡ በቈራጥነት ፡ ገጠሟቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ማናቸውንም ፡ የማሻሻል ፡ ፕሮግራማቸውን ፡ የሚፈጽሙበት ፡ ዘዴ ፡ ይታያቸው ፡ ነበር ። ዐዋቂ ፡ አማካሪዎችም ፡ ነበሯቸው ፤ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ በመልክም ፡ የምናስታውሳቸው ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ነበሩ ።

---

4.—የግሪክ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የአሪስጣስንና ፡ የተከታዮቹን ፡ የሰማዕታትነትን ፡ ሞት ፡ በያመቱ ፡ ታከብራለች ፡ በጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ።

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያ ፡ ከአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ ዕረፍት ፡ በኋላ ፡ ብሔራዊ ፡ የኾነ ፡ የጵጵስና ፡ ደረጃ ፡ እንዲቋቋምና ፡ አለቃውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ እንዲኾን ፡ ጠየቀች ። ይህ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ጸንቶ ፡ የቈየው ፡ ሞግዚትነት ፡ እንዲሻር ፡ የሚጠይቀው ፡ ጥያቄ ፡ ተቃዋሚ ፡ ድምፅን ፡ ከማሰማቱ ፡ በቀር ፡ ሰውም ፡ አሳበረ ፤ ጥንታዊው ፡ ልማድ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የሚሉትን ፡ ኹሉ ፡ አስከተተ ። የግርማዊነታቸው ፡ የማይታጠፈው ፡ ፈቃዳቸው ፡ ግን ፡ ኹሉንም ፡ አስታገሠው ። የመርከቡን ፡ መምሪያ ፡ ይዘው ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ ድንጋይና ፡ ቋጥኝ ፡ መካከል ፡ እየመሩና ፡ በጥንቃቄ ፡ እያዘዋወሩ ፡ መርከቡ ፡ በሰላም ፡ በጤና ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግን ፡ ያውቁበት ፡ ነበርና ።



በጃንሆይ ፡ ሜዳ ፡ በጥምቀተ ፡ ባሕር ።

የማሻሻሉ ፡ ክርክር ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ነበር ፤ ኢትዮጵያ ፡ በግምት ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ያለባት ፡ የክርስቲያናዊ ፡ መንግሥት ፡ ሀገር ፡ ናት ። ሀገሪቷም ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ የገባችው ፡ በራተኛው ፡ መቶኛ ፡ ዘመን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ገባች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባንድ ፡ አለቃ ፡ ብቻ ፡ ትተዳደር ፡ ማለትን ፡ አያስከትልም ፤ ይኸውም ፡ አንድ ፡ ጳጳስ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ እየተመረጠና ፡ እየተሾመ ፡ ይምጣላት ፡ ማለትን ፡ አያስከትልም ፤ ይኸውም ፡ አለቃ ፡



በቂ ፡ ያልኾነና ፡ የተገደበ ፡ ሥልጣን ፡ ይኑረው ፡ ማለትን ፡ አያስከትልም ፤ የምእመናኑን ፡ ቋንቋ ፡ ባህልና ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወግና ፡ ሥርዐትን ፡ የማያውቅ ፡ ይኹን ፡ ማለትን ፡ አያስከትምል ፤ ይህ ፡ አስተያየት ፡ የተገባ ፡ አይደለም ፤ ክርስቲያናዊ ፡ አይደለም ።

የተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ለክርክሩ ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ አዋልድ ፡ የኾነውን ፡ በኒቂያ ፡ በ፫፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰበሰበው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ደንግጎታል ፡ የተባለውን ፡ ድንጋጌ ፡ ነው ። ይህም ፡ ድንጋጌ ፡ የእስክንድርያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሞግዚትነት ፡ ለማጽናትና ፡ የበላይነቷን ፡ ለዘለዓለም ፡ ለማድረግ ፡ ታስቦ ፡ በሐሰተኛነት ፡ የተጨመረ ፡ ድንጋጌ ፡ ነው (5.) ።

---

5. —ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ የተባለው ፡ አብርሃም ፡ ኢኬሊንሲስ ፡ (ቀሲስ) ፡ የጻፈው ፡ ፵፪ኛው ፡ ቀኖና ፡ የሚባለው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ድንጋጌ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፓትርያርክ ፡ እንዳይመርጡ ፡ ይከለክላል ። ስኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ አለቃ ፡ የሚገባው ፡ ሥያሜ ፡ ካቶሊኮስ ፡ የመባል ፡ ማዕርግ ፡ ብቻ ፡ ኾኖ ፡ በእስክንድርያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይተዳደራል ፡ ይላል ። የድንጋጌው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ነው ።

«ኢትዮጵያውያን ፡ ፓትርያርክ ፡ ሊያቋቁሙና ፡ ፓትርያርክ ፡ ሊመርጡ ፡ አይችሉም ። ጳጳሳቸው ፡ በእስክንድርያ ፡ መንበር ፡ በተቀመጠው ፡ ፓትርያርክ ፡ ሥር ፡ ይተዳደራል ። ኾኖም ፡ ይኸው ፡ ጳጳሳቸው ፡ በነሱ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ፓትርያርክ ፡ ይቈጠራል ፤ ስመ ፡ ተጸውዖው ፡ ካቶሊኮስ ፡ ይኾናል ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ፓትርያርኮች ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊባል ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ የእውነተኛው ፡ ፓትርያርክ ፡ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ ስለሌለው ፡ ነው ። በሩም ፡ (ግሪክ-ቢዛንት) ፡ ማለት ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ ጉባኤ ፡ የተደረገ ፡ እንደኾንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፓትርያርክም ፡ የጉባኤው ፡ ተካፋይ ፡ የኾነ ፡ እንደኾን ፡ ይኸው ፡ ፓትርያርክ ፡ ከሴሉቂያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለጥቆ ፡ ሰባተኛውን ፡ ማዕርግ ፡ ይይዛል ። በሀገረ ፡ ስብከቱም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሾም ፡ የተፈቀደለት ፡ እንደኾን ፡ አንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ ሊያገባ ፡ አይችልም ። »

ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረታዊ ፡ አድርጎ ፡ መዝግቦታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ የኒቂያ ፡ ጉባኤ ፡ ከተሰበሰበበት ፡ ከ፫፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የተጻፈ ፡ የመኾኑን ፡ ምልክት ፡ ያሳያል ። የኒቂያ ፡ ጉባኤ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ጳጳስ ፡ አልነበራትም ። ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስም ፡ ስብከተ ፡ ጥምቀትን ፡ ገና ፡ መጀመሩ ፡ ነበር ። ስብከቱም ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ማግኘቱን ፡ ለቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ የነገረውና ፡ ላዲሶቹ ፡ የአክሱም ፡ ምእመናን ፡ ጳጳስ ፡ እንዲኾን ፡ የተመረጠውና ፡ ሥልጣን ፡ የተቀበለውም ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ነበር ።

ደግሞም ፡ ይህ ፡ መሠረቱ ፡ አዋልድ ፡ የኾነ ፡ ድንጋጌ ፡ ከታመነ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጳጳሳት ፡ እንደ ፡ ነበሩና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ የእስክንድርያን ፡ የበላይነት ፡ ለመሻር ፡ ይጣጣር ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ይኾናል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ድንጋጌው ፡ ከታመነ ፡ የፓትርያርክነት ፡ ማዕርግ ፡ ሙሉ ፡ ወግ ፡ ይዞ ፡ ነበር ፡ ማለትን ፡ ይኾናል ። በውነቱ ፡ ግን ፡ በኒቂያ ፡ ጉባኤ ፡ ጊዜ ፡ የፓትርያርክነት ፡ ማዕርግ ፡ ገና ፡ አልተረጋገጠም ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ተንቃፊ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሰባተኛው ፡ መቶኛ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ከስምንተኛው ፡ መቶኛ ፡ ዘመን ፡ መጀመርያ ፡ በፊት ፡ የተጻፈ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። ምናልባት ፡ እንዴት ፡ ሶርያዊት ፡ ቅብጣዊት ፡ ያዕቆባዊት ፡ ሲኖዶስ ፡ በሐሰተኛነት ፡ የጨመረችው ፡ ድንጋጌ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ።

www.ethiopianorthodox.org

የቀረው ፡ ቀርቶ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ አለቃ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ አባቶቹ ፡ አልጋ ፡ እንዲመለስ ፡ ከረዳት ፡ ከቤተ ፡ ሰሎሞን ፡ እንደራሴ ፡ ጋራ ፡ ባ፩ሺ፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባደረጉት ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ተነቃፊ ፡ ድንጋጌ ፡ አረጋግጠውለታል ፡ ተብሎ ፡ ይታመን ፡ ነበር ።

ተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ ፈለገ ፤ ግርማዊነታቸው ፡ ግን ፡ የዲፕሎማሲውን ፡ እርምጃና ፡ ችሎታን ፡ በመተማመን ፡ ከችኰላ ፡ አሠራርና ፡ ከኃይል ፡ አካሄድ ፡ በጥንቃቄ ፡ ርቀው ፡ ነገሩን ፡ በጠበቀ ፡ ዘዴ ፡ እያስታመሙ ፡ በዝግታ ፡ ከግባቸው ፡ ለማድረስ ፡ በራሳቸው ፡ ዐቅድና ፡ ስልት ፡ ተመሩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ንግግር ፡ ባ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተደረገው ፡ የግልግል ፡ ስምምነት ፡ ውሳኔ ፡ አገኘ ። አራት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ የተሾሙላት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዲሱን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከእስክንድርያ ፡ እንድትቀበል ፡ ስምምነት ፡ ተደረገ ። ባ፲፱፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፓትርያርኩ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዕጨጌ ፡ ሳዊሮስን ፡ ስለ ፡ ቀቧቸው ፡ የጳጳሳቱ ፡ ቊጥር ፡ አምስት ፡ ኾነ ።

ይህም ፡ ያምስት ፡ ጳጳሳት ፡ ሹመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንድትሾም ፡ ስለሚያስችላት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ነጻ ፡ ለመኾን ፡ ትሞክር ፡ ይኾናል ፡ የማለት ፡ ፍርኀትን ፡ በቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልብ ፡ አሳደረ ። ይህን ፡ ፍራቻ ፡ ለማስወገድና ፡ አዲስ ፡ አበባም ፡ ካይሮም ፡ የተነሣውን ፡ ጥርጥር ፡ ለማረጋጋት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ጳጳስ ፡ እንዳይቀቡ ፡ ቃል ፡ ገቡ ።

ቀጥሎም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጠላት ፡ ተወረረች ። የኢጣሊያም ፡ ኢትዮጵያን ፡ መያዝ ፡ በሁለቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መከከል ፡ የነበረውን ፡ መተሳሰሪያ ፡ በጠሰ ። ጣሊያኖች ፡ በዶዴካኔዝ ፡ ግዛታቸው ፡ ያላቸው ፡ የግሪክ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቊስጥንጥንያ ፡ ካለው ፡ ኤኩሜኒክ ፡ ፓትርያርክ ፡ በታች ፡ መሆኗ ፡ እንዲቀር ፡ ፈልገው ፡ ነጻ ፡ መንበረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንድታቋቁም ፡ ይገፋፉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ እንደዚሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የቅብጣውያን ፡ በታች ፡ እንድትኾን ፡ ላለመፈለግ ፡ የበለጠ ፡ ምክንያት ፡ ነበራቸው ።

ጣሊያኖች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመያዛቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የኤርትራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከነበረው ፡ ያውም ፡ ባዕድ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የበታች ፡ እንዳትኾን ፡ ከልክለው ፡ ሳለ ፡ ከቅብጦች ፡ ሥር ፡ መሆኗን ፡ በእርምሞ ፡ ፈቅደው ፡ ነበር ። ኢትዮጵያንም ፡ እንደ ፡



ኤርትራ ፡ በጃቸው ፡ ካገቡ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከቅብጣውያን ፡ ነጻ ፡ እንዲወጡ ፡ ለማድረግ ፡ ተጣጣሩ ። ኢጣሊያኖች ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ ያውቁ ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነጻነቱን ፡ ይወዳል ፤ ለመንግሥቱም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ነጻነትን ፡ ይፈልጋል ። በመገርመሪያዎቹ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ መንፈስ ፡ በማከባከብ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለማስተኛት ፡ እንዲያውም ፡ ለማፈን ፡ ሞከሩ ። ስለዚህ ፡ ነጻና ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማግኘት ፡ የነበራቸውን ፡ ምኞት ፡ አነቃቁ ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነጻ ፡ ናት ፡ ብለውም ፡ ዐወጁ ። በቀድሞው ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ተሾመው ፡ ከነበሩት ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ ሜትሮፖሊት ፡ (ሊቀ ፡ ጳጳሳት) ፡ ተባሉ ፤ ምክትልነቱን ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ተሾሙበት ። አፄር ፡ በነበረው ፡ በኢጣልያ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጳጳሳት ፡ ተቀቡ ።

እንደማይጠረጠረውም ፡ ይህ ፡ አሠራር ፡ ካይሮ ፡ ላይ ፡ የጋለ ፡ መቃወምንና ፡ ንዴትን ፡ ፈጠረ ። አዲሱ ፡ መንፈሳዊ ፡ አስተዳደር ፡ ተክዶ ፡ ያዲሱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ያዲሶቹም ፡ ጳጳሶች ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ተወገዘ ።

ሆኖም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባዲስ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ቆማ ፡ ተገኘች ። ይህ ፡ አዲስ ፡ ደረጃ ፡ ምንም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ሕጋዊ ፡ ባይኾን ፡ በጠቅላላው ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ ጋራ ፡ የተዋሐደ ፡ ነበር ።

በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከባርነት ፡ ቀንበር ፡ ወጥታ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ከዋና ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ከተገኙ ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ያዘ ። ብዙ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ጕዳዮች ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ ቃል ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ፤ ከነዚሁም ፡ አንዱ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ጕዳይ ፡ ነበር ። እንደ ፡ ተባለውም ፤ ምንም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የገዥነት ፡ ውሳኔያቸውን ፡ ለማስቀበል ፡ ችሎታ ፡ ቢኖራቸው ፤ ወይም ፡ ጣሊያን ፡ ያቈየውን ፡ አዲስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አድርጎ ፡ መቀበል ፡ መብታቸው ፡ ቢኾን ፤ የግርማዊነታቸው ፡ ሐሳብ ፡ ስለ ፡ ጕዳዩ ፡ ሊከተለው ፡ የፈቀደው ፡ አሠራር ፡ በሰላምና ፡ በመስማማት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችለውን ፡ ነበር ፤ በጕዳዩ ፡ የዲፕሎማሲ ፡ ስጦታቸውን ፡ አዋሉበት ። በፖለቲካ ፤ በኤኮኖሚ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚጠይቅ ፡ አያሌ ፡ ጕዳይ ፡ ቢኖርም ፡ የኢጣሊያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሰጡት ፡ ደረጃ ፡ በኋላ ፡ ለሚኾነው ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ጕዳይ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በተለይ ፡ ከማሰብ ፡ አልቦዘኑም ።

www.ethiopianorthodox.org

ልማድ ፡ ያቈየውንና ፡ አዋልድ ፡ የኾነውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመጥቀስ ፡ የካይሮ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ብዙ ፡ ተከራክረው ፡ ነበር ፤ ያዲስ ፡ አበባም ፡ በበኩላቸው ፡ ርትዕንና ፡ ያገሩን ፡ እርምጃ ፡ ተደግፈው ፡ አከራከረው ፡ የኒቂያ ፡ ድንጋጌ ፡ በሐሰተኛ ፡ የተሠራ ፡ መኾኑን ፡ በማስረዳት ፡ በብርቱ ፡ ተከራከሩ ።

አዲስ ፡ አበባም ፡ ካይሮም ፡ ያሉት ፡ ደንበኞቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስለ ፡ ጕዳዩ ፡ አጠንክረው ፡ ትግልን ፡ ገሠመሩ ። በሁለቱም ፡ ከተሞች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ጽሑፎች ፡ ተላለፉ ። ከኢትዮጵያም ፡ ከምድረ ፡ ምስርም ፡ መላክተኞች ፡ መጡም ፤ ኼዱም ። ንግግሩ ፡ ልክ ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ ሲቀርብ ፡ አዲስ ፡ ትብትብ ፡ ነገር ፡ ራሱን ፡ ብቅ ፡ አደረገ ። ግርማዊነታቸው ፡ ግን ፡ ትክክለኛና ፡ ክርስቲያናዊ ፡ የኾነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተያየት ፡ ተማምነው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በጥያቄያቸው ፡ ጸኑ ። ሐሳባቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሔንሪ ፡ ስምንተኛ ፡ ከካቶሊካዊው ፡ ፓፓ ፡ ቀሌሜንጦስ ፡ ሰባተኛ ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ክርክር ፡ ለመከተል ፡ አልፈለጉም ፡ ነበር ። ይፍጠን ፡ ይዘግይ ፡ እንጂ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ አስተያየት ፡ ድልን ፡ እንደሚያገኝ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ነበራቸው ። የቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ አስተያየት ፡ እውነተኛና ፡ ክርስቲያናዊ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድም ፡ ሕጋዊ ፡ መኾኑን ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ። በመንፈሳዊ ፡ ሕግ ፡ ነገሩ ፡ የማያስኬድ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ እንኳ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ "ሰንበት ፡" ለሰው ፡ ተፈጠረ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ለሰንበት ፡ አልተፈጠረም ፡ (ማርቆስ ፡ ፪ ፡ ፳፯) ፡ በማለት ፡ ወንጌልን ፡ ሊጠቅሱ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ በበኩሉ ፡ ምንም ፡ ቢኾን ፡ ወደ ፡ ቀድሞው ፡ የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ተመልሶ ፡ አይገባም ፡ ነበር ። የቀረው ፡ ቢቀር ፡ ይህ ፡ የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ በጣሊያን ፡ ጊዜ ፡ ተፍቋል ። በንግግሩና ፡ በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ በመለያየት ፡ እንቍረጠው ፡ የሚሉ ፡ ቍርጠኞች ፡ ተነሥተው ፡ ነበር ። ግርማዊነታቸው ፡ ግን ፡ የተነሣውን ፡ ማዕበል ፡ በታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ አበረዱት ፤ በከፍተኛ ፡ ብልኅነትም ፡ የተቃዋሚዎቹን ፡ ተከራካሪነት ፡ አለዘቡት ።

ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቅብጥ ፡ ፓትርያርክና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መልክተኞች ፡ መካከል ፡ የተፈረመው ፡ ስምምነት ፡ የንግግሩና ፡ የክርክሩ ፡ መደምደሚያ ፡ ኾነ ። ስምምነቱም ፡ ፓትርያርኩ ፡ ራሳቸው ፡ ወዲያውኑ ፡ አምስት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ይቀብሉ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስፈላጊ ፡ የሚኾኑትን ፡ ያኽል ፡ ጳጳሳት ፡ ይቀብል ፤ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ተመልሰው ፡ በመንበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ምትካቸው ፡ ከኢት



ዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ውስጥ ፡ ይመረጣል ፤ እሱም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለፓትርያርኩ ፡ እያስታወቀ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ያኽል ፡ ጳጳሳት ፡ ለመቀብት ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል ፡ የሚል ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ባረፉ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ የሚኾኑ ፡ መራጮች ፡ ባሉበት ፡ ጉባኤ ፡ ተሰብስበ ፡ ጳጳሱን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስን ፡ ምትክ ፡ አድርጎ ፡ ሾመ ። የብፁዕነታቸው ፡ ሥርዐተ ፡ ሢመት ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ካይሮ ፡ ላይ ፡ ኾነ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተጠመቀችበት ፡ ከ፫፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ክህናት ፡ የተመረጡ ፡ የራሷን ፡ ተወላጆች ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ጳጳሳት ፡ አገኘች ።



ብፁዕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከብፁዓን ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስና ፡ አቡነ ፡ ኒቆላኦስ ፡ ጋር ።

ይህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ደርሶ ፡ የማያውቀው ፡ ኹኔታ ፡ በጋለ ፡ ደስታ ፡ ተመረቀ ። አዲሱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከካይሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲገቡ ፡ በአይሮፕላን ፡ ማረፊያና ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ እንደ ፡ ድል ፡ በዓል ፡ ነበረ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰልፍና ፡ በመድፍ ፡ ሰላምታ ፡ ተቀበሏቸው ፤ ሕዝቡም ፡ በየመን

ገዱ ፡ ዳር ፡ ተሰልፎ ፡ ደስታውን ፡ በዜማና ፡ በእልልታ ፡ ገለጸ ። በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የሹመት ፡ በዓል ፡ ተሰናድቶ ፡ ነበር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ አዲሱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለመቀበል ፡ ከዙፋኑ ፡ አዳራሽ ፡ ቆመው ፡ ይጠባበቃሉ ። ከዙፋኑ ፡ በስተግራ ፡ የመንግሥቱ ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንትና ፡ ሚኒስትሮች ፡ ቆመዋል ። በስተቀኝ ፡ ደግሞ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ እንደራሴ ዎችና ፡ የግሪክ ፡ አርቶዶክስ ፡ ፓትርያርክ ፡ እንደራሴ ፡ የአክሱም ፡ ሜትሮ ፖሊት ፡ አባ ፡ ኒኮላኦስ ፡ ቆመዋል ፤ በዓሉ ፡ የማይረሳ ፡ ነበር ።

ግርማዊና ፡ ግርማዊት ፡ እስከ ፡ አዳራሹ ፡ ምድራኽ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ተቀበሏቸው ።

በዚህ ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ የተነገረውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ የዚህ ፡ ጽሕፈት ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገን ፡ አሳትመነዋል ። ይህ ፡ ቀን ፡ ያዲስ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ ቀን ፡ ሁኖ ፡ ዋለ ። አለመሰልቸታቸው ፤ ቈራጥነታቸውና ፡ ብልኀነታቸውም ፡ የፈጠረው ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ታላቅ ፡ ክብረት ፡ ተሰምቷ ቸው ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ የባረከው ፡ ተግባር ፡ ነበር ። ለመላው ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የደስታው ፡ ቀን ፡ ነበር ። ያለፈው ፡ ትውልድ ፡ ተመኝ ቶት ፡ የነበረው ፡ ደረሰ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያገሩን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ አገኘ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ በነጻ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገኘ ። ቈራጥነት ፡ ብልኀነትና ፡ አለመሰልቸት ፡ ከእምነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍሬን ፡ ሰጡ ።

የአንድ ፡ ሺ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሞግዚትነት ፡ መሻሩ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነጻነቷን ፡ ማግኘቷ ፤ እልቅናው ፡ በሀገር ፡ ተወላጅ ፡ የኾነ ፡ ብሔ ራዊ ፡ የጵጵስና ፡ ሥርዐትና ፡ ደረጃ ፡ መቋቋሙ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ የተወ ደደውን ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤላቸውን ፡ የምናከብረው ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድካማቸው ፡ ፍሬ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሁን ፡ የያዘችው ፡ አዲሱ ፡ ደረጃ ፡ ራስን ፡ ከማስተዳደር ፡ በላይ ፡ የኾነ ፡ ደረጃ ፡ ነው ፤ በሙሉ ፡ ነጻ ፡ ከመኾን ፡ ደረጃ ፡ ሊቈጠር ፡ ብዙ ፡ አይቀረውም ። በሕግ ፡ አገባብ ፡ ባይኾን ፡ እንኳ ፡ (De jure) በነገሩ ፡ ኹኔታ ፡ (De facto) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኾናለች ።



አዲሱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ካህናት ፡ መካከል ፡ እጅግ ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው ። ቅንና ፡ ደግ ፡ ናቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮ ጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የጠበቀ ፡ ቅናት ፡ አላቸው ። ያባትነት ፡ ጥረታ ቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሁሉም ፡ ሀይነት ፡ ህላዌ ፡ ደር ጅታ ፡ ለተቀበለችው ፡ አደራ ፡ በቂ ፡ እንድትኾን ፡ ነው ። ምንም ፡ የብፁዕ ነታቸው ፡ ቀጥሬታቸው ፡ ከቀድሞው ፡ ትውልድ ፡ ቢኾን ፡ መንፈሳቸው ፡ ማሻሻልን ፡ ይፈቅዳል ።



ብፁዕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዙፋን ፡ አዳራሽ ፡ በተደረገላቸው ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ቃል ፡ ሲናገሩ ።

አገራቸው ፡ በተወረረ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሌሞዊ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናቸውና ፡ ለሀገራቸው ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሥታቸው ፡ ታማኝ ፡ ኾነው ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ተከትለው ፡ ተሰደዱ ። አጥቂነትን ፡ ለመቃወም ፡ ለማይደመሰሰውና ፡ ለማይ ታጠፈው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ መንፈስ ፡ እንደራሲው ፡ ነበሩ ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነትም ፡ ልትኰራ ፡ ይገባታል ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያኗና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ላገሯ ፡ አያሌ ፡ አዲስ ፡ ሰማዕታት ፡ አበርክታለች ፤ እነአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፣ እነአቡነ ፡ ሚካኤል ፣ የደብረ ፡ ሊባኖስና ፡ የመናገሻ ፡ እልቂት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብርና ፡ ኵራት ፡ አስገኝተዋል ።



ብፁዕ ፡ ሰማዕት ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስና ፡ ብፁዕ ፡
የአክሱም ፡ ሜትሮፖሊት ፡ አቡነ ፡ ኒኮላኦስ ።



ኢትዮጵያን ፡ ከጠላት ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ትግሉ ፡ ሲገርመር ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሚባሉበት ፡ ጊዜ ፡ በየጦር ፡ ሜዳው ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ተከትለዋል ። በቀድሞው ፡ ዘመን ፡ እስራኤል ፡ ከአማሌቃውያን ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ሙሴ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርግቶ ፡ እንደ ፡ ጸለየ ፡ ሁሉ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስም ፡ የኢትዮጵያን ፡ አጥቂ ፡ ስለሚወጉት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ እጃቸውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርግተው ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ። ግርማዊነታቸው ፡ አሚድላ ፡ ላይ ፡ ያቆሙትን ፡ የነጻነት ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ባረኩ ። እግዚአብሔርም ፡ ያገልጋዩን ፡ ልመና ፡ ተቀበለ ፤ ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸውና ፡ ላገራቸው ፡ የነበራቸውን ፡ ታማኝነት ፡ ባረከ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ነጻነት ፡ በተደረገው ፡ ክርክር ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በሚገባ ፡ ተካፋይ ፡ ሁነው ፡ ነበር ፤ ጊዜውም ፡ ሲደርስ ፡ ልዑል ፡ ጌታችን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ የመጨረሻውን ፡ ከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ሰጣቸው ። ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀዳሚ ፡ የሀገር ፡ ተወላጅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አደረጋቸው ።

አዲሱ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስከትለው ፡ ሥራና ፡ ኃላፊነት ፡ ምንኛ ፡ ከባድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ያውቃሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ማሻሻልን ፡ የሚያፈቅረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድጋፍ ፡ ሆኗቸዋል ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ድጋፍ ፡ ይዘው ፡ ኃይሉ ፡ በድካም ፡ በኾነው ፡ አምላክ ፡ እምነታቸውን ፡ አጽንተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማደራጀት ፡ በሙሉ ፡ መንፈሳቸው ፡ ተነሥተዋል ። ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ረዳቶች ፡ ጳጳሳት ፡ አሏቸው ። «አዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ባሮጌ ፡ ዝቃት ፡ አያስቀምጡም ፡ ......አዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ባዲስ ፡ ዝቃት ፡ ውስጥ ፡ ያስቀምጣሉ ፤ ሁለቱም ፡ ይጠበቃሉና ፡ » (ማቴዎስ ፡ ፱ ፡ ፲፯) ፡ የሚለውን ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ይከተላሉ ።

ለታደሰችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ አካኼድ ፡ አዲስ ፡ ሠራተኞች ፡ በጥንቃቄ ፡ ያሠለጥናሉ ፤ ሐሳባቸውም ፡ ያዲሱን ፡ ዘመን ፡ እርምጃ ፡ ለመከታተል ፡ የሚችሉ ፡ ካህናት ፡ ለማበርከት ፡ ነው ።

ከፍ ፡ ካለው ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ርዳታ ፡ በቀር ፡ የሐረር ፡ ጳጳስ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፊሎስ ፡ የቅርብ ፡ ረዳታቸው ፡ ናቸው ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጥንታውያን ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መካከል ፡ የሚገባትን ፡ ሥፍራ ፡ እንድትይዝ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይደክማሉ ።

ሐሳባቸውንም ፡ የሚፈጽሙባቸው ፡ ብዙ ፡ መሣሪያዎች ፡ አሏቸው ። ትጋትና ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ በነጻ ፡ ሀገር ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ እን

www.ethiopianorthodox.org

ድትገኝ ፡ ከደረገት ፡ ከገናናው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚፈልቀው ፡ እንቂ ፡ መንፈስ ፡ ነው ።

እሊህ ፡ ገናና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከፈጸሚቸው ፡ አስደናቂና ፡ የማይረሱ ፡ ከሚኸኑት ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ይህች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዘመናት ፡ በኋላ ፡ ነፃነቷን ፡ እንድታገኝ ፡ ያደረገት ፡ ነው ።

በመላው ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ታላቁን ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ እንደሚያስታውሱት ፡ ሁሉ ፡ መጪው ፡ ትውልድ ፡ እሊህን ፡ ገናና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በጠበቀ ፡ ምስጋና ፡ ያስታውሳቸዋል ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ምሥራቃዊት ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታላቁን ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ እንዳንድ ፡ ሐዋርያ ፡ ታከብረዋለች ።

ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ አይገባቸውምን ?

አባ ፡ ኒቆላኦስ ፡
የግሪክ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ የአክሱም ፡ ሜትሮፖሊት ።



www.ethiopianorthodox.org

## የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ንግግር ።

### ጃንሆይ ፤

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕድል ፡ በሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ማዕርግ ፡ እድገት ፡ አግኝቶ ፡ ለዚሁም ፡ ዕድል ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኜ ፡ በመገኘቴ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግነዋለሁ ።

### ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ የመባልን ፡ ዕድል ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ የወሰደችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖትና ፡ የምግባር ፡ ባለቤት ፡ በመሆኗ ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ሀብትን ፡ አጣምራ ፡ ይዛ ፡ ስትሠራበት ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ደርሳለች ።

የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ለሥጋ ፡ ደካማነት ፡ ኃይልን ፡ ስለሚሰጠው ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብትና ፡ ሥጋዊ ፡ ሀብት ፡ ተደጋጋፊዎች ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉ ።

ኢትዮጵያ ፡ በፊት ፡ በኦሪት ፡ በኋላም ፡ በወንጌል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምልኮ ፡ ተቀብላ ፡ ስታምን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ ቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ባንድ ፡ ልቡና ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብለውታል ።

ኢትዮጵያ ፡ በደጋጎቹ ፡ በአብርሃና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመን ፡ የክርስቶስ ፡ ብርሃን ፡ ስለ ፡ በራላት ፡ የመጀመሪያውን ፡ መሪዋን ፡ ሰላማን ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ አሰኝታዋለች ። እሷ ፡ በክርስቶስ ፡ ልብሰ ፡ ብርሃን ፡ የተጐናጸፈች ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ሁና ፡ በሷ ፡ ደግሞ ፡ ሐዋርያዋ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ በመባሉ ፡ ማኅቶተ ፡ ብርሃን ፡ ተቀባይ ፡ የሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለወንጌል ፡ ስብከት ፡ ዘይትና ፡ ፈትል ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝለት ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡ መጀመሪያ ፡ ተቀባይ ፡ በመሆናቸው ፡ ይህን ፡ ከብርሃን ፡ የተወረሰ ፡ ስም ፡ አትርፈዋል ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ኅጽዋ ፡ ለህንደኬ ፡ የተባለው ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገደኛ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነገረውን ፡ የኢሳይያስን ፡ ተፈጻሚ ፡ ትንቢት ፡ በሐዋርያው ፡ በፊልጶስ ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ሳይጠራጠር ፡ ማመኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ «ሳያዩኝ ፡ ያመኑብኝ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው» ፡ የተባለውን ፡ ብፅዕና ፡ ተቀባይ ፡ መሆኗን ፡ ያስረዳል ።

ወንጌል ፡ በኦሪት ፡ ተተክታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከተስፋፋች ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ በጳጳስ ፡ በኩል ፡ መብት ፡ እንዲኖራት ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሳያደርግ ፡ አልቀረም ።

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ በመቅረቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙውን ፡ ዘመን ፡ በዚያው ፡ በቈየው ፡ ልማድ ፡ ስትተዳደር ፡ ኖረች ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተሾመላት ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ ሥራዋን ፡ መቀጠሏ ፡ አልቀረም ።

በፈቃደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳን ፡ ጳጳስ ፡ ለመሆን ፡ የበቁት ፡ ታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሆናቸውን ፡ ስናገር ፡ መንፈሳዊው ፡ ብርሃናቸው ፡ በሁላችን ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ እያልሁ ፡ ነው ።

ያቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክ ፡ በጭሩ ፡ ሳስታውስ ፡ አባትዎ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋሉላት ፡ ውለታ ፡ አብሮ ፡ ይታሰበኛል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕዝባቸው ፡ አስተዳደር ፡ የብርሃን ፡ መሣሪያዎች ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በኩል ፡ የመንፈስ ፡ መሪዎች ፡ ሁነው ፡ የሠሩትን ፡ መልከም ፡ ሥራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አትዘነጋውም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ከመገርመሪያው ፡ አባትዎ ፡ ከዳዊት ፡ ቀጥሎም ፡ ከሰሎሞን ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የመከከለኛውንና ፡ ያሁኑኛውን ፡ ኂሩታዊ ፡ ምግባር ፡ ስናመዛዝነው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋለላትና ፡ የፈጸመላት ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ተመስጋኙ ፡ ሥራዎ ፡ ይገልጸዋል ።

ከጥንት ፡ ገምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ መገናኛ ፡ ሳይለወጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባትን ፡ ለማግኘት ፡ የቻለችው ፡ በግርማነትዎ ታጋሽነት ፡ ነው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «በመታገሥና ፡ በሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ተጠበቀልን ፡ ተስፋ ፡ እንገሥግሥ ፤ » (ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፩) ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ በመከተል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ይኸን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መንፈሳዊ ፡ እድገት ፡ ለማስገኘት ፡ ቻለ ።

እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ «እኔ ፡ ላንተ ፡ ጋሻ ፡ ነኝ ፤ ዋጋህም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ » (ዘፀ ፡ ፲፭) ፡ ያለውን ፡ የፈጸመልዎ ፡ ይህን ፡ መልከም ፡ ፈቃድዎን ፡ ተመልክቶ ፡ ነው ።



የኢትዮጵያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውለታዎን ፡ የማትዘነጋ ፡ በመሆኗ ፡ በምትጸልየው ፡ ጸሎትና ፡ በምታቀርበው ፡ መሥዋዕት ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሥቷ ፡ ሕይወትና ፡ ስለ ፡ ሕዝቧ ፡ ደኅንነት ፡ ተከላካይ ፡ በመሆኗ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘረጋችው ፡ እጅዋ ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ሳያገባላት ፡ ቀርቶ ፡ አያውቅም ።

ባለፈው ፡ በመከራችን ፡ ሰዓት ፡ ሞቱን ፡ ሕይወት ፡ መራራውን ፡ ጣፋጭ ፡ ከባዱን ፡ ቀላል ፡ አድርገው ፡ የተቀበሉትን ፡ የመንፈሳውያን ፡ አርበኞች ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስንና ፡ አቡነ ፡ ሚካኤልን ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ እናስታውሳችው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋሉላትን ፡ ውለታ ፡ በመገንዘብና ፡ ስለ ፡ እውነት ፡ መሥዋዕት ፡ መሆን ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ የሚገባቸውን ፡ ፈጸሙ ።

እነግረከሙ ፡ አኀዊነ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ የተናገረውን ፡ ስናስብ ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ባ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥርዐተ ፡ ሢመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተሰብስበን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገልንን ፡ ደስታ ፡ አብረን ፡ ስንከፈል ፡ በግርማዊ ፡ ቃልዎ ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ታላቅነትና ፡ የሥልጣኔ ፡ እድገት ፡ ከሃይማኖት ፡ ትልቅነቷ ፡ ጋር ፡ የተባበረ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል» ፡ ብለው ፡ በተናገሩት ፡ መሠረት ፡ የሃይማኖቷ ፡ እድገት ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ መንፈሳዊ ፡ መብት ፡ አስገኘ ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የቈየውን ፡ መንፈሳዊ ፡ መገናኛ ፡ በመጠበቅ ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አስገኘ ። ይህንም ፡ የጋራ ፡ ደስታ ፡ አብሮ ፡ በመከፈል ፡ በምድረ ፡ ግብጽ ፡ ብፁዕ ፡ ዳግማዊ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ያደረጉልኝን ፡ ደግነትና ፡ አቀባበል ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ አስበዋለሁ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉዳይ ፡ ከመጨረሻው ፡ ግብ ፡ አድርሷል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማዕርጓ ፡ በማደጉ ፡ መጠን ፡ አላፊነቷ ፡ እንዲሁ ፡ እያደገ ፡ መሄዱን ፡ ተረድተነዋል ። የተደከመበትን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያድርግ ። የግርማዊነትዎን ፡ ዘር ፡ ይባርክ ፤ ዙፋንዎ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲተላለፍ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኑር ።

ከኢትዮጵያ ፡ ከገራችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በረከትና ፡ ረድኤት ፡ አይለይ ፤ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

የክቡር፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስትር፡ ቢትወደድ፡ መኰንን፡ እንዳልካቸው፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በዚህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ እንድናገር ፡ ፈቃድ ፡ በማግኘቴ ፡ የተሰማኝን ፡ ደስታ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የብዙ ፡ ዘመን ፡ ምኞቷ ፡ ተፈጸመላት ። ለጥንታዊነቷም ፡ የተገባውን ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ አገኘች ።

የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገና ፡ ከሕፃንነቷ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እየጠበቁ ፡ ያሳደጓትን ፡ የነገሥታት ፡ አባቶችዎን ፡ አርአያ ፡ በመከተል ፡ የማይናወጥ ፡ የክብር ፡ መንበር ፡ ስለ ፡ መሠረቱላት ፡ ለጃንሆይ ፡ የደረሰው ፡ ዕድል ፤ ለአብርሃና ፡ ለአጽብሐ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ዕድል ፡ ጋራ ፡ የተካከለ ፡ ነው ። ለነጻዩቱ ፡ አገሬ ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስፈልጋታል ፡ በማለት ፡ አስበና ፡ አርቆ ፡ ተመልክቶ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከዛሬ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የጣለው ፡ መሠረት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለታወቀው ፡ ክብሯና ፡ ስሟ ፡ የተገባውን ፡ የተቀደሰ ፡ የነጻነትን ፡ መብት ፡ አስገኝላት ።

ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሲታሰብ ፡ ሁለት ፡ ችግሮች ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እነሱም ፡ መጀመርና ፡ መጨረስ ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሀብቶች ፡ ዕድልዎ ፡ ሆነው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፥ በዘመንዎ ፡ ተጀምሮ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜውን ፡ ያላገኘ ፡ አንድም ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የለም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ጥንታዊ ፡ ወጉንና ፡ ሥርዐቱን ፡ ጠብቆ ፡ የኖረውን ፡ ሕዝብዎን ፡ ያዲሱ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኔ ፡ ያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ ለማድረግ ፡ ኑሮውን ፡ በሀብት ፡ ለማደርጀትና ፡ በጥበብ ፡ ለማደላደል ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ዘዴ ፡ ትምህርትን ፡ ማስፋፋት ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ትጋት ፡ ያደረጃቸው ፡ የተማሩ ፡ ልጆች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቀዋሚ ፡ ዕድል ፡ ለመስጠት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በሰፊው ፡ ለሚደከመው ፡ ሥራ ፡ ዋና ፡ ረዳት ፡ ለመሆን ፡ ችለዋል ።

ማንኛውንም ፡ የተገኘውን ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ጠቃሚ ፡ የሚያደርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ መሆኑ ፡ በሕፃናቱ ፡ አእምሮ ፡ እንዲቀረጽ ፡ ለማድረግ ፡ በየጊዜው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሚሰጠው ፡ ምክር ፡ የኅሊና ፡



ምስክርና ፡ ወቃሽ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ስለሚመራቸው ፡ እርምጃቸው ፡ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሏል ።

«ሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ ካመነ ፡ ሥልጣኔው ፡ የደኅንነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ሊሆንለት ፡ ይችላል» ፡ ሲል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ የሌለበት ፡ ሥልጣኔ ፡ አጥፊ ፡ መሆኗን ፡ አስረድቷል ።

ይህም ፡ እየተደጋገመ ፡ በሥራ ፡ የተመሰከረ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ በዕውቀቱና ፡ በጥበቡ ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለማወቅና ፡ ለመመርመር ፡ ችሏል ። ራሱን ፡ ግን ፡ ለመመርመርና ፡ ለማወቅ ፡ የሚችለው ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ብቻ ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ከበጎ ፡ ምግባር ፡ ከራቀ ፡ በኋላ ፡ ጥበቡም ፥ ዕውቀቱም ፥ ሀብቱም ፡ ከጭንቅ ፡ ሊያድነው ፡ እንደማይችል ፡ የዛሬው ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ያስረዳል ።

ያገርን ፡ ነጻነትና ፡ ክብርን ፡ ሕይወትን ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሕዝብዎ ፡ የሥልጣኔ ፡ እድገት ፡ ዘላቂ ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ከመንፈሱ ፡ እድገት ፡ ጋራ ፡ ትይዩ ፡ ሆኖ ፡ ሲሄድ ፡ መሆኑን ፡ በማስተዋል ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ በሆነው ፡ ታሪካዊ ፡ ዘመን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስገኝላት ፡ መብት ፡ የዕድልን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትዕግሥትና ፡ ዕውቀት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ ያላትን ፡ ጥንታዊ ፡ መገናኛ ፡ ሳታቋርጥ ፡ የጠየቀችውን ፡ መብት ፡ በስምምነት ፡ እንድታገኝ ፡ መደረጉ ፡ በሁለቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መካከል ፡ የጠበቀ ፡ ዝምድና ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ታሪክዎን ፡ ዘወትር ፡ ከፍ ፡ ያደረገው ፥ ሥራዎን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቸርነትና ፡ ረድኤት ፡ በታች ፡ በመጣልና ፡ የኔ ፡ ድካም ፡ ምንም ፡ አያደርግም ፥ ሁሉንም ፡ የሚፈጽም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለትዎ ፡ ነው ። በሥራና ፡ በድካም ፡ የተገኘ ፡ እውነተኛ ፡ ደስታ ፡ ዘላቂ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ዕድል ፡ አያቋርጥም ። ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የጀመረ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ይጨርሳል ፡ ተብሏል ። እግዚአብሔር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርምጃ ፡ ያቃና ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ።
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ።
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

www.ethiopianorthodox.org

## የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቃል ።

በዘመናችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ከሰብንባቸውና ፡ ከሠራናቸው ፡ ነገሮች ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ አድርገን ፡ የምንቈጥረው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመሾሙ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ድካማችንን ፡ ለባረከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

ይህም ፡ ዛሬ ፡ ተፈጽሞ ፡ የምናየው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራሷን ፡ የሚያስችል ፡ ሥራ ፡ ከተጀመረበት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ እንሥቶ ፡ ጉዳዩ ፡ እያደገ ፡ እንዲሄድና ፡ እዚህ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የነበረውን ፡ ድካም ፡ ያለፈበትን ፡ መንገድ ፡ ስናስብ ፡ የከባድነቱ ፡ ታላቅነት ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ።

አሁን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጽም ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፡ ነጻ ፡ ሕዝባችንና ፡ መንግሥታችን ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲኖራቸውና ፡ በዓለምም ፡ እንዲታወቅ ፡ አደረገ ።

ይህም ፡ በዘመናችን ፡ ስለ ፡ ተፈጸመልን ፡ እኛም ፡ ሕዝባችንም ፡ የምንከሎራበት ፡ ነው ።

ያለፉት ፡ አባቶቻችን ፡ ነገሥታቶች ፡ ይህን ፡ ተመኙ ፤ በተስፋም ፡ ተመለከቱት ፤ በሃይማኖት ፡ የጸናችም ፡ ተስፋ ፡ በዘመናችን ፡ ስትፈጸም ፡ ለማየት ፡ አበቃን ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለና ፡ ለተቀደሰ ፡ ሥራ ፡ በዘመናችን ፡ ጀማሪ ፡ ለመሆን ፡ መልካሙ ፡ ዕድል ፡ ስለ ፡ ደረሰዎ ፡ ደስታችንን ፡ እንገልጥልዎታለን ።

በዚህም ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ የግብጽና ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በበለጠ ፡ የሚከባበሩበትና ፡ የሚተማመኑበት ፡ አዲስ ፡ ዘመን ፡ ተከፈተ ።

ይህም ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተገለጠላቸው ፡ ብሩህ ፡ በሆነ ፡ የመገባባት ፡ መንፈስ ፡ በበኩላቸው ፡ ለረዱ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ ለተቀመጡ ፡ ለብፁዕ ፡ ዳግማዊ ፡ ዮሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንገልጣለን ።

በዘመናችንና ፡ በዘመናቸውም ፡ ለተፈጸመው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻል ፡ ዕድላቸው ፡ ከዕድላችን ፡ ጋራ ፡ መግጠሙን ፡ ስና



ስብም ፡ ደስ ፡ ይለናል ። መንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ለሆነው ፡ ለሰው ፡ ለዓለማዊና ፡ ለሰማያዊ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሁለቱም ፡ ዓለም ፡ ጎዳና ፡ መሪው ፡ ነው ።

በመንፈሳዊ ፡ ኃይልም ፡ መሪነት ፡ ሰው ፡ የተቀደሰ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሊደርስበት ፡ ከሚገባው ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ለዓለም ፡ ቍስል ፡ የመንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ መድኃኒትና ፡ መዳኛ ፡ እንዲሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ባለባት ፡ መጠን ፡ ከሚደርስብዎ ፡ ታላቅ ፡ ሸክም ፡ በቀር ፡ በተለየ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተግባሩን ፡ ለማደርጀት ፡ ሰማያዊ ፡ መንገዱን ፡ ለማቅናት ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ አላፊነት ፡ በብፁዕነትዎ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋና ፡ ኃይል ፡ እንዲረዳዎ ፡ ከልባችን ፡ እንመኝልዎታለን ።

www.ethiopianorthodox.org